# የፖሊሲ መግለጫ

**Ethiopian Economics Association (EEA)**

*Professionalism and Economic Thinking for Development!*

**ቁጥር 10 / ሰኔ 2017 ዓ.ም**


## Vision

The EEA is envisioned to become a premier economics association in Africa by 2030.

## Mission

The mission of EEA is to provide a platform for networking, access to information and learning; to contribute to a better understanding of the global, national and local economic issues; to inform and influence economic policymaking and investment decision; to offer training and foster the advancement of the discipline of economics.

## Values

Professionalism, integrity, independence, quality, efficiency, inclusiveness, teamwork, accountability and transparency.


Copyright © Ethiopian Economics Association

**Disclaimer:** The views and opinions expressed in this publication are those of the authors and do not necessarily reflect the official policy or position of the Ethiopian Economics Association. Readers are encouraged to verify the information independently and seek professional advice where necessary. The authors will not be held liable for any loss, damage, or inconvenience caused because of the use or reliance on the content of this publication.


# የሙስና ባህርያት በኢትዮጵያ


**ደግዬ ጎሹ**[1]

**አረጋ ሹመቴ**[2]

**ደምረዉ ጌታቸዉ**[3]



## ማጠቃለያ

ሙስና ከኢኮኖሚ ዕድገትና ደኅንነት እስከ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ድረስ ዘርፈ ብዙ መዘዝ አለው። መተማመንን ይቀንሳል፣ ተቋማትን ያዳክማል፣ ገበያ ያዛባል፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገትን ያደናቅፋል። የአገልግሎት ቅልጥፍና ማዳከም ብሎም ማሳጣት፣ ወጪ መጨመር፣ ድህነትን መጨመር እና የሀብት እና የአገልግሎት ክፍፍል ፍትሃዊ እንዳይሆን ማድረግ የሙስና ዋና ዋና መገለጫዎች ናቸዉ።

ይህንን ችግር ለመፍታት በክልል፣ በአገር አቀፍ እና በአለም ዓቀፍ ደረጃ በርካታ የህግ እና የቁጥጥር ማዕቀፎች እንዲሁም ስምምነቶች ተዘጋጅተዋል። ይሁን እንጂ በርካታ የፀረ ሙስና ፖሊሲዎች፣ ሕጎችና ተቋማት ተግባራዊ ቢደረጉም በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የሙስና ስርጭት እየጨመረ ነው። ይህ አጭር የፖሊሲ መግለጫ በመንግስት አደራ በተሰጣቸው አካላት መካከል ያለውን የሙስና መጠን እና ተሳትፎ እንዲሁም ኢትዮጵያ በመንግስታዊ ሙስና (Public sector corruption) እና በዘርፈ-ብዙ ሙስና (multidimensional corruption) ያላትን አንፃራዊ ቦታ ይገመግማል።

ባለፉት አስርት አመታት በአለም ዓቀፍ ደረጃ በመንግስት የስራ ዘርፍ ሙስናን ለመዋጋት የተደረጉ ጥረቶች በአብዛኛው ከሽፈዋል። በአለም ዓቀፍ ደረጃ 90 በመቶ የሚሆነው ህዝብ ከፍተኛ እና በጣም ከፍተኛ ሙስና እንዳለ ሲገነዘብ በኢትዮጵያ ደግሞ ይህንን የሚገነዘቡት 86.5 በመቶ ናቸው። የክልል እና የአካባቢ ባለስልጣናት፣ የንግድ ስራ አስፈፃሚዎች እና የህዝብ አገልግሎት ሰጭዎች በአብዛኛው እንደ ሙሰኛ ተደርገው ይታያሉ። ከ50% በላይ የሚሆኑት ኢትዮጵያውያን አብዛኞቹ በመንግስት አደራ የተሰጣቸው አካላት ሙሰኞች ናቸው ብለው ያምናሉ። በኢትዮጵያ የመንግስት ዘርፍ ውስጥ የተደራጀ ሙስና መስፋፋቱ ውጤታማ ካልሆኑ የፀረ-ሙስና ህጎች ጋር ተዳምሮ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት እና አስተዳደርን በእጅጉ እንዲገታ አድርጎታል። ይህም የፀረ-ሙስና ፖሊሲዎችን እና ተቋማትን ማደስ እና ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አጉልቶ ያሳያል።



[1] PhD, Director, Research and Policy Analysis: e-mail: degyeabgos@gmail.com

[2] PhD, Senior Researcher

[3] Research Project Coordinator

## 1. የጥናቱ ዳራ

ሙስና በአለም አቀፍ ደረጃ ከግለሰቦች ዝንባሌ እና በግለሰቦች ከሚከናወኑ ተግባራት በላይ ብዙውን ጊዜ የግል ጥቅምን መነሻ ባደረገ መልኩ ወደ ስርአታዊ ወይም መንግስታዊ ሙስና የተሸጋገረ ሆኗል። ይህ አይነቱ ሙስና፥ በአስተዳደርና ተቋማት ድክመት፣ በኢኮኖሚ እኩልነት እጦት እና ድህነት፣ በግልጸኝነትና ተጠያቂነት እጦት፣ በፖለቲካ አለመረጋጋት እና ግጭት፣ እንዲሁም በስልጣን/በኃይል ኢ-ሚዛናዊነትን እና በመሳሰሉት የሚያባብስ ውስብስብ ጉዳይ ነው።

ስርዓታዊ ሙስና የማይገታ ከሆነ በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ዘርፈ ብዙ አሉታዊ ተጽዕኖ የማምጣት አቅም አለው። በኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖው ሙስና የኢኮኖሚ ዕድገትን ይገታል፣ የሀብት ድልድል ኢ-ፍትሃዊነትን ያባብሳል፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍና ያሰተጓጉላል፣ የመዋዕለ ነዋይ ፍሰትን (ኢንቨስትመንትን) ይቀንሳል። በፖለቲካዊ መልኩ በመንግስት ላይ እምነት እንዲጠፋ፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት እንዲፈጠር እና የስልጣን ጥመኛነት ስር እንዲሰድ ያደርጋል። በማህበራዊ ደረጃ የህዝብ አገልግሎቶች መበላሸት፣ የማህበራዊ ደንቦች እና እሴቶች መሸርሸር እና የድህነት መጨመርን ያስከትላል። በተፈጥሮ ሀብት እና ከባቢ ላይ ሙስና የአካባቢ መራቆትን እና የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲዎች መጣስን ያስከትላል።

ስር የሰደደ ሙስና በአጠቃላይ የሀገር እድገት መቀንጨርን ያስከትላል። ስለዚህ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ ተገቢ የመፍትሄ ሃሳቦችን በሳይንሳዊ ዘዴ መለየት እና ተግባራዊ ማድረግ በጣም ወሳኝ ነው። ለዚህም ውጤታማና አውድ-ተኮር መፍትሄዎችን ለመጠቆም ጉዳዩን በጥልቀት መመርመር አስፈላጊ በመሆኑ ይህንን የምርመር ስራ ማካሄድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

## 2. የሙስና ሁኔታ በኢትዮጵያ

ይህ የፖሊሲ አጭር መግለጫ ሦስት የሙስና መለኪያዎችን በመጠቀም ዋና ዋና ግኝቶችን ያቀርባል። እነዚህም የመንግስት ዘርፍ ሙስና (corruption perception index) የሙስና ደረጃ (level of corruption) እና የባለብዙ ገፅታ ሙስና መረጃ ጠቋሚ (multidimensional corruption index) ናቸው። እነዚህን መለኪያዎች በመመርኮዝ ኢትዮጵያ ከአለም አማካይ ሁኔታ ጋር ያላት ነባራዊ ሁኔታ በንጽጽር ቀርቧል።

### 2.1. የመንግስታዊ ሙስና (Public sector corruption) በኢትዮጵያ

የዚህ አይነቱ ሙስና ስፋት እና ጥልቀት በክፍላተዓለም መካከል በእጅጉ ይለያያል። ምዕራብ አውሮፓ ሀገራት በአብዛኛዉ በዚህ አይነት ሙስና ብዙም የማይታሙ ሲሆን፤ ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሀገራት፣ ምስራቅ እና መካከለኛው እስያ እና መካከለኛው ምስራቅ እና ሰሜን አፍሪካ (MENA) ሀገራት እንደ ቅደም ተከተላቸው በሙስና የተዘፈቁ ናቸው። ጥናቱ እንደሚያመለክተዉ የአለም አቀፍ መንግስታዊ ሙስና በአንፃራዊነት ባለፉት አመታት ብዙም መሻሻል አልታየበትም።

በኢትዮጵያ የሚስተዋለዉ የመንግስታዊ ሙስና ከሰሃራ በታች ካሉት የአፍሪካ ሀገራት አማካኝ ጋር ሲነፃፀር በተወሰነ ደረጃ የተሻለ ነዉ። ጥናቱ እንደሚያመላክተዉ፥ በኢትዮጵያ የመንግስታዊ ሙስናን በመቆጣጠር ረገድ እ. ኤ. አ. እስከ 2021 ድረስ መሻሻል ታይቷል። ሆኖም ከ2021 እስከ 2023 ድረስ የሙስና መጠኑ በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መጥቷል። እ.ኤ.አ. በ2023 ኢትዮጵያ በ37 በመቶ የሙስና እይታ ግምት (corruption perception index) ከአለም በ98ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች። ይህም እጅግ ከፍተኛ የሆነ የሙስና ደረጃን ያሳያል። ከ2019 ጀምሮ የተስፋፋው የሃገር ውስጥ ግጭቶች እና የፖለቲካ አለመረጋጋት ለብልሹ አሰራር እና ለሙስና ማደግ ምቹ ሁኔታን እንደፈጠረ ይታመናል።

### 2.2. የሙስና መጠን በኢትዮጵያ

በዓለም ዙሪያ በአጠቃላይ የሙስና ደረጃ ከፍተኛ ወይም በጣም ከፍተኛ መሆኑን በአብዛኛዎቹ (90 በመቶ በሚሆኑት መላሾች) የሚታመን ሲሆን 45 በመቶ የሚሆኑት መላሾች በጣም ከፍተኛ ነዉ ብለዉ ያምናሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ በተካሄደዉ የቁልፍ መረጃ አቀባዮች ዳሰሳ መሰረት 76.3 በመቶ የሚሆኑት ምላሽ ሰጪዎች ሙስና በጣም ከፍተኛ ነው የሚለውን ይቀበላሉ። ይህም በኢትዮጵያ ያለው የሙስና ደረጃ ከዓለም አቀፉ አማካኝ ጋር ሲነጻጸር በ31.3 በመቶ ከፍ ያለ መሆኑን ያመለክታል። በኢትዮጵያ ውስጥ 8 በመቶ የሚሆኑት ምላሽ ሰጪዎች መካከለኛ ሙስና መኖሩን ሲያምኑ፥ 11.2 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ከፍተኛ ሙስና መኖሩን ይቀበላሉ። በአጠቃላይ እነዚህ ውጤቶች እንደሚያሳዩት ሙስና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተንሰራፍቶ የሚገኝ ኩነት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። እ.ኤ.አ. በ2020 ኢትዮጵያ በአጠቃላይ በ85.65 የሙስና ደረጃ ውጤት በማስመዝገብ ከአለም 15ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች። ይህም ኢትዮጵያን ከፍተኛ ሙስና ከሚስተዋልባቸዉ ሀገራት ተርታ ያስመድባታል።

የጥናቱ አንኳር ዉጤት እንደሚያመለክተዉ ኢትዮጵያ በጣም ከፍተኛ የሙስና ደረጃ ቢኖራትም በክልሎች መካከል ያለዉ የሙስና ስርጭት መጠነኛ ልዩነት አለዉ፡፡ በቀድሞው የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሙስና ከፍተኛ ቢሆንም በሌሎች ሁሉም ክልሎች ደግሞ መጠኑ ከ80 በመቶ በላይ በመሆኑ በጣም ከፍተኛ እንደሆነ ተመላክቷል። በተለይ በከተሞች መካከል ባለ ንጽጽር በድሬዳዋ በአዲስ አበባ እና በሐረሪ ከተሞች ሙስና በጣም ከፍተኛ ነው። በአጠቃላይ ይህ የሚያሳየው በኢትዮጵያ ያለው ሙስና በአጠቃላይ በክልሎችም ሆነ በከተማ አከባቢዎች በጣም ከፍተኛ መሆኑን ነው።

## 2.3. ዘርፈ ብዙ ሙስና በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሙስና ያለው እይታ በዓለም ዙሪያ ካለው እይታ ጋር ይስማማል። በዓለም ዙሪያ በጥናቱ ከተሳተፉ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች (ምላሽ ሰጪዎች) በተገኘ መረጃ እና የትንተና ዉጤት መሰረት እጅግ አብዛኞቹ (85.6 በመቶ) አብዛኞቹ (63.7 በመቶ) ወይም ሁሉም (21.9 በመቶ) የሚሆኑት የክልል እና የአካባቢ ባለስልጣናት፣ የንግድ ስራ አስፈፃሚዎች እና ጋዜጠኞች በሙስና ውስጥ እንደሚሳተፉ ያምናሉ። በተመሳሳይ መልኩ 80.4 በመቶ ኢትዮጵያውያን እነዚህ ቡድኖች አብዛኞቹ ወይም ሁሉም በሙስና የተዘፈቁ ናቸው ብለው ያስባሉ። እ.ኤ.አ. በ2020 ኢትዮጵያ በ59.7 በመቶ ዘርፈ ብዙ የሙስና አመላካች ውጤት (MCI) ከአለም 35ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች። ይህም በሀገሪቱ ውስጥ እንዲያገለግሉ እምነት የተጣለባቸው አካላት አብዛኞቹ በሙስና የተዘፈቁ መሆናቸውን ያሳያል።

በአለም አቀፍ ደረጃ 65 በመቶ የሚሆኑት የመንግስት ባለስልጣናት በሙስና ውስጥ በአንፃራዊነት ከፍተኛ ተሳትፎ እንዳላቸዉ ያሳያል። ከዚያም የንግድ ሥራ አስፈፃሚዎች (63.4 በመቶ) እና የአካባቢ ባለስልጣናት (63.3 በመቶ) ከፍተኛ ሙስናን በማስተናገድ ይከተላሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲያገለግሉ አደራ የተሰጣቸው አካላት በሙስና ውስጥ የሚያደርጉት ተሳትፎ ከአለም አቀፋዊ አማካይ የተለየ አይደለም። ይሁን እንጂ በክልል ባለስልጣናት (63.8 በመቶ)፣ በአካባቢ ባለስልጣናት (63.6 በመቶ) እና በንግድ ሥራ አስፈፃሚዎች (62.3) ዘርፈ ብዙ የሙስና አመላካች ዉጤት በማስመዝገብ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከተመዘገበዉ (59.9 በመቶ) ዉጤት ብልጫ ወስደዋል። ይህም በግልጽ የሚያመለክተዉ በመንግስት ሹማምንት የሚፈጸመዉ ሙስና ላቅ ያለ እንደሆነ ነዉ።

# 3. የፖሊሲ ምክረ ሀሳቦች

ሙስና በተለያዩ ዘርፎች ኢኮኖሚን የሚጎዳ አለማቀፋዊ ተግዳሮት እንደሆነ እሙን ነዉ። ይሁን እንጂ በዓለም አቀፍ ፥ በአገር አቀፍ፣ በክልል ደረጃ ሙስናን ለመዋጋት የተደረገው ጥረት ውጤት አልባ ሆኖ ተገኝቷል። ባለፉት ዓመታት በዓለም ዙሪያ መንግስታት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ሙስናን ለመዋጋት ተነሳሽነት ቢያሳዩም የሙስና መጠን ወይ ጨምሯል ወይም ብዙም ሳይቀየር ቆይቷል።

በተጨባጭ ማስረጃዎች ላይ በመመርኮዝ ይህ ጥናት ሙስናን ለመዋጋት የሚከተሉትን እርምጃዎች ጨምሮ ዘርፈ-ብዙ እና የተሰናሰሉ ቁርጠኛ ወሳኔዎችን መዉሰድ እንደሚያስፈልግ ይመከራል።

- **የግንዛቤ ማስጨበጫ፡-** ሳይንሳዊ መረጃ እና ማስረጃዎችን ብሎም ማሳያዎችን በማጣቀስ የፀረ-ሙስና ዘመቻዎችን በማህበረሰብ ደረጃ ግንዛቤ እንዲኖር ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻ ማካሄድ ያስፈልጋል።
- **ተቋማትን ማጠናከር፡-** ሙስናን ለመከላከልና ለመዋጋት የሚያስችሉ ጠንካራ፣ ግልጽ እና ተጠያቂነት ያላቸውን ተቋማት መገንባት ያስፈልጋል። ለዚህም ተግባራዊነት ከሰዉ ንክኪ የጸዱ የመንግስት አገልገሎቶችን ማስፋት፥ የግሉ ዘርፍ በአገልግሎት ዘረፉ ተሳታፊ እንዲሆን ማስቻል ይገባል።
- **የህግ ማሻሻያ፡-** ጠንካራ የፀረ-ሙስና ህጎችን እና መመሪያዎችን ተግባራዊ ማድረግ እና ማስከበር ያስፈልጋል።
- **ግልጸኝነትን ማሳደግ፡** የሙስና እድሎችን ለመቀነስ በመንግስት እና በንግድ ስራዎች ላይ ግልጸኝነትን ማሳደግ ያስፈልጋል። የዲጂታል አማራጮችን በመጠቀም መረጃን እና ንግድ ነክ የሆኑ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎችን ለተጠቃሚዉ ማድረስ እንደ አንድ አማራጭ ሊወሰድ ይችላል።

- **የሲቪል ማህበረሰብን ማብቃት፡-** የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን እና ሚዲያዎችን በመደገፍ ባለስልጣናት ተጠያቂ እንዲሆኑ እና የታማኝነት ባህልን እንዲያጎለብቱ ማበረታታት ያስፈልጋል።
- **የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፡-** የኢትዮጵያ መንግስትና ፀረ-ሙስና ኤጀንሲዎች ሙስናን በመዋጋት ረገድ በየደረጃው ያሉ ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ አለባቸው። ሙስናን በመዋጋት ረገድ የህዝብ፣ የግሉ ዘርፍ፣ የሲቪክ ማህበራት፣ የሃይማኖት ተቋማት እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትን ለማሳተፍ ደግሞ ደጋፊ የህግ እና የቁጥጥር ማዕቀፍ ያስፈልጋል።

**ሙስናን መዋጋት የሁሉንም ህብረተሰብ ክፍሎች ቁርጠኝነትን እና ትብብርን የሚጠይቅ የረዥም ጊዜ ሂደት ነው።**

## 4. ዋቢዎች


Alcazar, L R. Andrade. (2001). Diagnosis corruption. pp.135 ISBN 978-1- 931003-11-7.

Dong, B, Torgler B. (2010). The consequences of corruption: evidence from China, Fondazione Eni Enrico Mattei (FEEM), Institutions and Markets Papers No. 91006.

Myint, U. (2000). Corruption: causes, consequences and cures, *Asia-Pacific Development Journal,* 7(2).

TI (Transparency International). (2023). Corruption Perception Index (2012-2023).

World Bank Group. (2022). Worldwide Governance Indicators (WGI).



Further inquiries and information:

Email: info@eea-et.org

Website: http://www.eea-et.org

https://facebook.com/EEAEthio

https://twitter.com/EthioEconAssoc

https://www.youtube.Ethiopian Economics Association

Ethiopian Economics Association
Lemi Kura Sub-city, Woreda 13
CMC area adjacent to St. Michael Church

Tel: +251-11 - 645 32 00/645 30 76/ 645 30 41

P.O.Box 34282,

Addis Ababa, Ethiopia


### Conflict of Interest

There is no conflict of interest between researchers.